# ለተቃውሞ ትግሉ ስኬት የኢትዮጵያውያን
# ተቀራርቦ አብሮ መስራት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው

ምስክር ከLA <misekir@yahoo.com>

ማንነቴን ደግሜ በመፈተሽ ለዚህ ጽሁፍ ያነሳሳኝና ሁኔታዎችም ከፈቀዱ ወደ እንቅስቃሴ እስከመግባትም እንዳስብ ያደረገኝ በአቶ ጃዋር ሲራጅ መሃመድ Tigrean Nationalism: From Revolutionary Force to Weapon of Repression በሚል ርእስ የጻፉት (http://www.abugidainfo.com/?p=13075) ጽሁፍ ነው ።

በእነአቶ መለስ የወያኔ/ኢህአዴግ አመራር እየተደቆሰች ያለችውን ሐገራችንን በዚሁ ስርአት ስለደረሰባት እና እየደረሰባት ስላልው በደል በመዘርዘር የአንባቢዬን ጊዜ ማባከን አልፈልግም። በመጀመሪያ የራሴን ማንነት በመግለጽ አንባቢዬ ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ ለምን እንደተነሳሳሁ ይረዳልኝ ዘንድ እራሴን ላስተዋውቅ።

እኔ በትውልዴም በስሜቴም ኢትዮጵያዊ ነኝ። ከዚህ ባለፈ ደግሞ አባቴ የአክሱም እናቴ የሰሜን ሸዋ ተወላጅ ናቸው። ተወልጄ ያደኩት በአዲስ አበባ ከተማ ነው። ከኢሕአዴግ በፊት ቀደም ባለው ጊዜ እስከማስታውሰው ድረስ ከልጅነት የመጀመሪያ ድግሪዬን እስክያዝኩበት ዘመን ያባት የናቴ ዘር ጉዳይ ብዙም አሳስቦኝ አያውቅም ነበር። እንደመታደልም ሆኖ እናቴና አባቴ እስክዛሬም በምወደውና በማምንበት ለልጆቼም ለማስተላለፍ በምተጋበት እምነትና ጥሩ ፍቅር ነበር ያሳደጉኝ።

ወደ ዋናው ጉዳዬ ስመለስ አቶ ጀዋር ከላይ በጠቀስኩት ጽሁፋቸው ያነሱዋቸውና የተነተኑዋቸው የትግራይ ተወላጆች የዘመኑ ችግር የኔን ከፍተኛ ትኩረት የሳበ ጉዳይ ነው። ይህንንም ስል በትግራይ የዘር ሀረጌ ምክንያት የደረሱብኝን ምስቅልቅል ጉዳዮችና ፈታኝ ገጠመኞች እርሳቸው በበቂ ትንታኔ ቁልጭ አድርገው ያስቀመጡት ስለሆነ በእኔ በጀማሪው የፖለቲካ ትንታኔ መነካካትና ማቆሸሽ አልፈልግም። እዚህ ላይ ግን እርሳቸው በጽሁፋቸው መደምደሚያ ላይ እንደገለጹት በዘር ሀረግ የትግራይ ተወላጆችን ከዘራችን በፈለቁ አምባገነኖች በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ እያደረሱ ስላለው ጥፋት በተለያዩ ምክንያቶች እያሣየን ያለነውን ዝምታ ፤ ከዚያም ባለፈ አሁንም በተለያዩ የጥቃት መረቦች ምክንያቶች (አቶ ጀዋርን ጽሁፍ ይመለከቱ) በመያዝ ሳንወድ የወያኔ/ኢህአዴግን ስርአት አማራጭ የሌለው የመኖር ህልወናችን አድርገን እየኖርን ላለን ዜጎች የሃላፊነት መሸሻና መሸፈኛ ላደርግው አልፈልግም።

የአቶ ጀዋር ጽሁፍ በግልጽ እንዳስቀመጠውና በኔም አመለካከት ትክክል ሆኖ የማየው የትግራይ ተውላጆች የወያኔ ጉዳት ሰለባዎች ነን የሚል ትልቅ እምነት አለኝ። ይህንን ስል ወያኔ የትግራይን ህዝብ ዘርህ ነኝ በማለት ለራሱ ስግብግብ አላማ ማራመጃነት ድጋፍ እንዲሆኑት ሲል ለትግራይ አላዳላም ትኩረትም ጥቅምም አልሰጠም ያሚል ጭፍን አመለካከት የለኝም። ነገር ግን እንደኔ አመለካከት ወያኔ ለትግራይ ልጆች የወጠነው መረብ፦

1ኛው. በህይወቴም ጭምር እንደምመሰክረው የትግራይ ትወላጆችን ኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ውስጥ እንዲያስገባ የታቀደና በሌሎች ኢትዮጵያውያን አእምሮም ይኸው ጉዳይ ጥያቄ እንዲያጭር ተደርጎ የተቀመረ የዘመናችን አስከፊ ክስተት ነው።

2ኛው. አሁንም በአቶ ጀዋር ማጠቃለያ እንደተገለጸው በሚያሳዝን ሁኔታ የዚሁ አምባግነን ስርአት ጥፋቶች ሁሉ ተጠያቂነትን በትግራይ ልጆች ላይ እንዲወድቅ የማድርጉ ስራ ነው። ከዚህም በተያያዥነት በመሳሪያ ሀይል ብቻ ስልጣንን የሙጥኝ ያለው ይኸው በህዝብ የተጠላ ስርአት በማይቀር ሞቱ ጊዜ መሪዎቹ የቀረ ዘመናችውን በተድላ ለማሳልፍ የተዘጋጁና ለቀረነው ግን ከሌሎች ወገኖቻችን ጋር እንዳንኖር በክፉም አይንም እንድንታይ የተደረገው ሰይጣናዊ ዝግጅት ነው።

እዚህ ላይ ይህን አጭር ጽሁፍ ስጽፍ ለአንባቢዎች ልገልጽ የምወደው እኔና ቤተሰቤ በፈጣሪ ቸርነት ከሃገር ወጥተን በአሜሪካን ሀገር በአካባቢያችን ከሚገኘው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ራቅ ብለን እየኖርን መሆናችንን ነው። ልጆቼን ከምወዳቸውና በመልክም በእምነትም ከሚመስሏቸው ወንድሞችና እህቶች ራቅ አድርጌ ማሳደጌ ለኔ እናቴና አባቴ እንዳስተማሩኝ ሁሉ ለልጆቼ የማስተምራቸው የማንነት ጉድለት እንደሚያስከትል ሳይሰማኝ ቀርቶ አይደለም። የኔ ከኢትዮጵያውያን ሽሽት በዘር መጠርጠር ብቻ አይደለም ይልቁንም ለሆዳቸው ካደሩ ሰላይ ዘመዶቼም የመሸሽ ሀሳብ ጭምር እንጂ።

ውድ ወገኖቼ ለአቶ ጀዋር ምስጋና ይድረሳቸውና ኮርኩረው እንዳናገሩኝ ዛሬን ወያኔ ያበላሸው ቢመስልም እንኳ እኔ አቶ ጅዋር እና ሌሎቻችንም በአስተዋይነትና በመተማመን የነገን የሃገራችንን ተስፋ በቅድሚያ ከነዚህ ስጋ ከለበሱ መጥፎ መንፈሶች ለማስጣል ቀጥሎም ሁላችንም በማንነታችን ኮርተን ልንኖርባት የምታስችለንን ሀገር ለመመስረት ቢያንስ እንኳን የጋራ የምክክር መድረክ መመስረት እንዴትና ለምን ያቅተናል? በተለይ በተለይ ይህ ጉዳይ ለኛ ለወያኔ መቀለጃ ለሆነው ለዲያስፓራዎች ከብዶን ነው? ለመሰባሰብስ የስርአቱ ተቃዋሚነት ብቻ እንኳ የሚያገናኘን በቂ መክንያት አይሆነንምን? የዚህ ስርአት ተቃዋሚ ኢትዮጵያዊያን ፓርቲዎችስ እኔን ደግፉ እኔን ብቻም ስሙኝ ከማለት ሳይቃጠል በቅጠል አትሉም? እየደረሰስ ባለው ከአንድ ብሄር ጋር የተቆራኘ የሀገር ጥፋትና የታሪክ ተወቃሽነትስ ለመዳን በተቃውሞ ትግሉ መትጋት የበለጠ ከማን ይጠበቅ ይሆን?

ወገኖቼ እኔ በራሴ ይህን "የከፋፍለን የበልተን እናጥፋው" ስርአት ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ እንዲሉ የታይታ ባልሆነ የሀገርና የወገን ፍቅር ለመዋጋትም ሆነ ምሽጉ ሆኜ ላልደብቀው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ጋር በመሆን ሀገርንና ወገንን ከበልጠ አደጋ ለመታደግ እንድሰራ ቃል እየገባሁ የቃሌም ሰው ያድርገኝ እላለሁ እርስዎስ?

ምስክር ከ LA